# ሲፒጄ– መብት ጠባቂ ወይስ የሀገራት ደረጃ አፅዳቂ?

**ሰለሞን በቀለ** 05/15/13

ከመሰንበቻው አይጋ ፎረም የተሰኘውና የኢትዮጵያ ጉዳዮች በስፋት የሚንሸራሸሩበት ድረ-ገፅ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴርን በመጥቀስ አንድ መግለጫ አስነብቦን ነበር– በሽብርተኝነት ወንጀል ተከስሰው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ያፀናባቸውን እነ አቶ እስክንድር ነጋንና አቶ አንዱዓለም አራጌን እንዲሁም ሌሎች ተከሳሾችን የተመለከተን ጉዳይ። መግለጫው የፍትህ ስርዓቱን ማኮሰስ ለፕሬስ ነፃነት የሚፈይደው ነገር የለም ባለው ርዕሱ፤ እንደ ሲፒጄ ዓይነት የሀገሪቱን ፍርድ ቤቶች ነፃ አሰራርን በጣልቃ ገባዊ አካሄድ ለመጋፋት የሚሞክሩ አካላት ተግባራቸው የሀገራችንን ሉዓላዊነት መዳፈር መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ አትቷል።

እርግጥም ሰሞኑን የተከሳሾቹን የፍርድ ሂደት በተመለከተ የሀገራችንን ፍርድ ቤቶች ነፃነትን በመደፍጠጥ በሂደቱ ጣልቃ ለመግባት ያልሞከረ ኒዮ-ሊበራል ተቋም አለ ለማለት አያስደፍርም። በተለይም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚከናወኑ ማናቸውም ነገሮች ትክክል የማይመስሏቸው እና ስያሜያቸውና ተግባራቸው ለየቅል የሆኑት እንደ ጋዜጠኞች መብት ተከላካይ ነኝ ባዩ ሲፒጄን፣ ሂዩማን ራይትስ ዎችንና ፍሪደም ናውን የመሳሰሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ቡድኖች፤ ከርዕዮተ-ዓለም ልዩነታቸው በመነሳት ግለሰቦቹ በተከሰሱበት የሽብር ወንጀል የስር ፍርድ ቤት (ከፍተኛው ፍርድ ቤት) የሰጠውን ብይን ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በማፅናቱ ሳቢያ የተለመደ ፀረ-ኢትዮጵያ መዝሙራቸውን ከማሰማት በዘለለ ማስጠንቀቂያ እስከ መስጠትም ደርሰዋል።

በተለይም አክራሪው ኒዮ ሊበራል ተቋም ሲፒጄ የሀገራችንን ፍርድ ቤቶች የአሰራር ነፃነት እጅግ በሚያስገርም ሁኔታ በመጋፋት በአፍሪካ ዳይሬክተሩ ሞሐመድ ኬይታ አማካኝነት "…ውሳኔው የሽብርተኝነትን ከባድ ወንጀል ያሳነሰ፣ በፖለቲካ ተነሳሽነት የተሰጠውን የይምሰል ፍትሕ የደገፈ እንዲሁም የኢትዮጵያን ዓለም አቀፍ ደረጃ የቀነሰ ነው።…የኢትዮጵያ መንግስት እስክንድርን ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሊለቅ ይገባል" ብሏል። ይህ የፅንፈኛው ቡድን አባባል ቢያንስ በሶስት ምልከታዎች ሊታይ የሚችል ነው። አንደኛው የሀገራችንን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ያጣጣለ ሲሆን፤ ሁለተኛው የኢትዮጵያን ፍርድ ቤቶች አሰራርን ነፃነት የሌለው አስመስሎ ማቅረቡ ነው። ሶስተኛው ደግሞ ቡድኑ ከጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ወደ ሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ መዳቢነት ከመሸጋገር ባለፈ፤ ለይስሙላም ቢሆን የሚያራግበውን የስራ ገደብ ዘሎ አንድን ሉዓላዊት ሀገር በመዳፈር ማስጠንቀቂያ ቢጤ በመስጠት በሀገራችን ፍርድ ቤቶች ጥፋተኛ መሆኑ የተረጋገጠበትን ግለሰብ በአስቸኳይ እንዲፈታ ለማዘዝ መሞከሩ ነው። ታዲያ እነዚህን ሶስት

የተቋሙን ነውረኛ አባባሎች በዝርዝር ከመመልከታችን በፊት ቡድኑ ስለተሟገተለት አቶ እስክንድር ነጋ ጥቂት ግንዛቤ መያዝ አስፈላጊ ይመስለኛል።

አቶ እስክንድር በምርጫ 97 ወቅት ከቅንጅት ነውጠኛ አመራሮች ጋር በማሴር ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመናድ ባከናወኑት የጥፋት ተልዕኮ ተከስሰው ጥፋተኛ በመሆን ለሁለት ዓመታት መታሰራቸው ይታወሳል። ይሁንና በወቅቱ አቶ እስክንድርና መሰሎቻቸው ዳግም በእንዲህ ዓይነቱ ፀረ-ህዝብ ስራ ውስጥ እንደማይሰማሩ ገልፀውና ክስተቱን በድጋሚ ከፈፀሙ በህግ የተበየነባቸው ውሳኔ እንዲተገበር ተማፅነው መንግስት ይቅርታ እንዲያደርግላቸው በደብዳቤ ይጠይቃሉ። በዴሞክራሲያዊ መርህ የሚመራውና አንጻሩ እሴቱ የሆነውን መቻቻልን የሚያስቀድመው የሀገራችን መንግስትም፤ የእነ አቶ እስክንድርን የይቅርታ ደብዳቤ በመቀበል በህጉ መሰረት ከእስር እንዲፈቱ ይወስናል–ከጥፋታቸው ይማራሉ በሚል እሳቤ።

ይሁንና ነገሩ "ያደቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም" እንዲሉ በመሆኑ፤ አቶ እስክንድር ከእስር ከተፈቱ ወዲህ እንኳንስ ከጥፋተኝነታቸው ሊማሩ ቀርቶ ይባስ ብለው ግጭትንና ሁከትን ብሎም ግብረ-ሽበራን በሚቀሰቅሱ ተግባራት ላይ መሰማራትን ስራዬ ብለው ነው የተያያዙት። እንዲያውም ከእስር ከተለቀቁ ወዲህ በግልፅና በተዘዋዋሪ በምርጫ 97 ወቅት የጀመሩትን የሴራ ተልዕኮ ለመተግበር ይበልጥ ባተሌ ሆነው መክረማቸውን የዚህ ፅሑፍ አንባቢ የሚዘነጋው አይደለም። እርግጥም ሰውዬው ጥራዝ ነጠቅና ሴራን የሚዶልቱ ፖለቲከኛ ስለመሆናቸው የማያውቅ ሰው ያለ አይመስለኝም፡፡ የዚህች ሀገር እና ህዝቦቿ ለውጥና ዕድገት ፈጽሞ የማያስደስታቸው፤ በጥላቻ የተሞሉ፣ ጭፍን ፖለቲከኛ መሆናቸውንም ጭምር፡፡ ታዲያ በወቅቱ ይህን የለበሱትን የጭፍን ተቋዋሚነት ማዕረግ በግልፅ ደርበውት አደባባይ ለመውጣት አልፈለጉም፡፡ ይልቁንስ ሰውዬው በሐሰተኛ ማዕረግ እንዲጠሩ ነው የከጀሉት፡፡ ለዚህም ደግሞ ተመሳሳይ አቋም ባላቸው አንዳንድ የግል ሚዲያዎች "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" በሚል ዕውቅና ለማግኘት ያደረጉት ጥረት እንደ አንድ ማሳያ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን አንድ ዕንፈኛና ሁከት ናፋቂ እንዲሁም ከሀገሪቱ ህግ ውጭ እንዳሻው የሚፈነጭ ግለሰብ "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" ነኝ ብሎ ለመናገር ብቃቱም ሆነ ድፍረቱ ያለው አይመስለኝም፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን አቶ እስክንድር ራሳቸውን ለመደበቅ የተጠቀሙበት ዘዴ ልክ እንደ ዛሬው ተከራካሪያቸው ሲፒጄ ዓይነት ያለ ተግባራዊ ማንነት በሐሰት ስም መንቀሳቀስን ነው።

ዳሩ ግን የጋዜጠኛነት ሙያ ሰውዬው ከተዘፈቁበት የጥላቻ ፖለቲካ ገለልተኛ መሆንን ያዛል፡ ፡ ጋዜጠኛ ለህዝብ ጥቅም የሚሰራ እንጂ እንደ እርሳቸው በሰላም የልማት ተጠቃሚነቱን እያረጋገጠ ያለውን የሀገራችንን ህዝብ ወደ ብጥብጥና ሁከት ለመስደድ የሚጽጽጥ አይደለም፡፡ የሙያው ሥነ- ምግባርም እርሳቸው እውነትን ለመቅበር የሚያደርጉትን ዓይነት መፍጨርጨር በጽኑ

የሚቃወም ነው። እናም ግለሰቡ ሙያው ከሚጠይቃቸው መስፈርቶች አንዱን እንኳን ሳይዙ ራሳቸውን "ጋዜጠኛ" ብለው ሊሾሙ አይገባቸውም። ሌሎች አጫፋሪዎቻቸውም ቢሆኑ።

እኔም ሆንኩ ድፍን የኢትዮጵያ ህዝብ የአቶ እስክንድር ነጋን ማንነት ያውቃል ብዬ የማምነው ጋዜጠኛም፣ ተንታኝም ሆነ ጦማሪ አለመሆናቸውን ነው። ለዚህ ደግሞ ማስረጃ ፍለጋ ብዙ ርቀት መጓዝ የሚጠይቅ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ግለሰቡ ባገኙት አጋጣሚዎች ሁሉ ሲያሻቸው በስማቸው፣ ደስ ሲላቸው ደግሞ በብዕር ስማቸው ተጠቅመው የሚጽፏቸው ልቦለዳዊ ትረካዎች፣ የፅልመት ውሸከታዎች… ወዘተ. ከበቂ በላይ ማረጋገጫዎች በመሆናቸው ነው፡፡ ሰውዬው ከእስር ከተፈቱ በኋላ በተቃዋሚ ቡድኖች የበጀት ድጋፍ በሚታተሙ "ጋዜጦች" ላይ በነጻ አሊያም ከፍለውም ቢሆን የሚያሳትሟቸው የፈጠራ ስራዎች ዕውነታውን ፍንትው አድርገው ያሳያሉ– የእርሳቸውን ጨለምተኝነት፣ ከሃዲነት እና እብደት። ስለሆነም በእኔ እምነት እርሳቸውን "ጋዜጠኛ፣ ተንታኝና ጦማሪ" እያለ የሚጠራ ግለሰብ ወይም ቡድን አንድም ተሳስቷል አሊያም እያላገጠባቸው ይመስለኛል።

ታዲያ ውድ አንባቢዎቼ ይህንን ያልኩት በምክንያት ተመርኩዤ እንጂ ከመሬት ተነስቼ አለመሆኑን እንደምትረዱልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እርግጥም ሰውዬው ራሳቸው ከጻፏቸውና አስተሳሰባቸውን ካራመዱባቸው የፈጠራ ስራዎቻቸው ተነስቼ ላቀርባቸው የምችላቸው ምክንያቶች በርከት ያሉ ናቸው፡፡ ለአብነት ያህልም የግለሰቡን ማንነት በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችለን ዘንድ የአንድ ወቅት ጉዳዮችን የኋሊት መለስ ብዬ የትውስታዬን ጓዳ በመፈተሽ በጥቂቱ ማውሳት ይቻላል፡፡

የመጀመሪያው ማሳያዬ ከስሮ ከገበያ ውጪ የሆነው "አውራምባ ታይምስ" /ነፍስ ይማር ብያለሁ/ የነሐሴ 21 ቀን 2003 ዓ.ም ዕትም "ጋዜጣ" ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የስልጣን ጥም አንገብግቦት ሰሞኑን መድረክን የገመገመው አንድነት ፓርቲ ነሐሴ 29 ቀን 2003 ዓ.ም በፅህፈት ቤቱ ባካሄደው ስብሰባ ላይ እኚህ ሰው ያቀረቡት ፅሁፍ ነው። እዚህ ላይ አስቀድሜ ለአንባቢያን ለመጠቆም የምፈልገው ጉዳይ ግለሰቡ በሁለቱም ማሳያዎቼ ላይ ያቀረቧቸው ፅሁፎች ከቦታና ጊዜ ልዩነት ባለፈ የይዘት ልዩነት የሌላቸው መሆኑን ነው።ለምን ቢሉ "በጋዜጣው" ላይ የሰፈሩት የሰውዬው የሁከት ጥሪዎች ተሰብስበው በፓርቲው የስብሰባ መድረክ ላይ የቀረቡ በመሆናቸው፤ አንዱ ማሳያ ሌላውን የመግለፅ ሙሉ አቅም ይኖረዋል። በመሆኑም በተከታይነት የማነሳቸው "አውራምባ ታይምስ" ላይ የሰፈሩት ጉዳዮች አንድነት ፅህፈት ቤት ላይ የቀረበውን ፅሁፍ ይዘት የሚያንፀባርቅም ይሆናል።

በያኔው "አውራምባ ታይምስ" ጋዜጣ በፊት ለፊት ገጹ ላይ "ኢህአዴጎች አብዮቱ ወደ ኢትዮጵያ ይመጣል ብለው በአደባባይ ባያምኑም፤ ልቦናቸው ግን ያውቀዋል" የሚል አባባል በርዕስነት ሰፍሮ ነበር፡፡ በትልልቁ ተጽፎ ከሚታየው ከዚህ ጥቅስ ስር ደግሞ "እስክንድር ነጋ (ጋዜጠኛና ተንታኝ)" የሚል ነገርም ተቀምጧል፡፡ ሰውዬው ባርኔጣቸውን ደፍተው የተነሱት ፎቶ ግራፍም ከጥቅሱ በስተቀኝ በኩል በጉልህ ይታያል፡፡ በወቅቱ አባባሉን ከምንም በፊት ለማንበብ የፈለኩት

የሰውዬዉን ፎቶ በመመልከቴ ነበር፡፡ ግለሰቡ በጥላቻ የተወጠሩ በመሆናቸው "ዛሬ ደግሞ በምን ላይ ዘመቻ አድርገው ይሆን?" የሚለው አጓጊቶኝ ትኩረቴን በአባባሉ ላይ አደረኩ፡፡

በዚህ ርዕስ ላይ ያልገባኝ ነገር ቢኖር "...አብዮቱ ..." የሚለው ነበር፡፡ የትኛው አብዮት ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጣ ግልጽ የሆነልኝ ነገር ባይኖርም ሰውየው ሊነግሩን የፈለጉት አንድ አብዮት እንደሚኖር ግን አልተጠራጠርኩም፡፡ ይህን አባባል "እስክንድር ነጋ ነው ያለው?" የሚለው ነገርም አደናግሮኛል፡፡ ምክንያቱም ሰውየው "ጋዜጠኛና ምንትሴ ነኝ" ሲሉ ነበር የማውቃቸው ፡፡ ታዲያ ጋዜጣው በምንጭነት ሊጠቀምባቸው የሚችሉ የተሻሉ ግለሰቦችን አሊያም የተቃውሞ አታሞ ደላቂዎችን አጥቶ የራሱን ሪፖርተሮች በምንጭነት መጠቀም ጀመረ እንዴ?... የሚለውም ጉዳይ አግራሞትን ፈጥሮብኝ ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ ግን የዚህን ርዕስ ማብራሪያዎችን ሳየው ሁሉም ነገር እንደሚመለሰልኝ ገምቼ ዋናውን ጽሑፍ ለማንበብ ፈለግኩ፡፡... አነበብኩትም።...እስክንድር ነጋ ግን ከጋዜጠኝነት መሰረታዊ ተግባር ወጥተው እንዲሁም ትንታኔያቸውም የጨለምተኝነት ፖለቲካ ሙሉ በሙሉ አጥልቶበት አየሁ። እናም ሰውዬው የማምታቻ ስሞቻቸውን በአግባቡ መጠቀም ተስኗቸው ተመለከትኩ። በአጭር ቋንቋ ፋርሽ መሆናቸውን ተረዳሁ። መፎረሽ ብቻም ሳይሆን የሀገሪቱን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግን በመተላለፍ ዜጎችን ለአመፅ ሲያነሳሱ እንደነበርም ታዘብኳቸው–የ97 ዓ.ም. ቀጣይ የሴራ ዱለታቸውን።...ይህ ማሳያዬ 'ትውስታ አንድ' ተብሎ ሊገለፅ ይችላል።

ከጊዜው ርዝማኔ የተነሳ ምንም እንኳን ምልከታዬ የተሟላ ባይሆንም፤'ትውስታ ሁለትም' እንዲህ ነበር። እናም እስቲ ሰውዬው በዚያን ሰሞን በጋዜጠኝነት ጭንብል ተጀቡነው በእውነተኛው የተቃዋሚነት ስራቸው የተወራጩባቸውን አስገራሚ የትንቢት፣ የማስጠንቀቅና የለየለት የአመፅ ጥሪዎች በግርድፉ እነሆ ልበልዎ፡፡... "ኢህአዴግ ከሚቀጥሉት አምስት ዓመታ በፊት ሌላ ምርጫ ካላካሄደ ችግር ይገጥመዋል"፣ "ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጊዜያቸው ስላበቃ መውረድ አለባቸው" እና "የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች አመፁን ይቀስቅሱ" የሚሉትና በአቶ እስክንድር ‹‹ነውጥ ደማሪ›› ጭንቅላት የተደመደሙት ግላዊ እብደቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ታዲያ እኔም በወቅቱ 'ጎበዝ ነገሩ እንዴት ነው?... ጋዜጠኛና ተንታኝ ተብዬው ግለሰብ እንደ ፖለቲከኛ በራሳቸው ጊዜ ድምዳሜ እየሰጡ መለፈፍ ጀመሩ እንዴ? – ሌላው ቢቀር ግለሰቡ ራሳቸው የሚያምኑበት የምዕራቡ ዓለም ጋዜጠኝነት መሰረቶች የሚባሉት ሚዛናዊነትና ርቱዕነትን (balance and fairness) እንዲሁም ማህበራዊ ኃላፊነትን (Social responsibility) ምነዋ ዘነጉት?' በማለት ከራሴ ጋር ሙግት መግጠሜ አልቀረም። ...ምን ላድርግ?!... መቼም አንድ ጋዜጠኛ ነኝ ባይ ‹‹ተማሪዎች ለአመፅ ውጡ›› ብሎ በግላጭ ከቀሰቀሰ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን በግል ‹‹ባስቸኳይ ይውረዱ!›› ብሎ ካስጠነቀቀ እና የሚንቀሳቀስበትን ህገ-መንግሥታዊ ስርዓቱን ተፃርሮ ‹‹ሌላ ምርጫ ይካሄድ!›› ካለ እርግጥም በማን አለብኝነት ከህግ በላይ ሆኖ እየፈነጨ ነው ማለት ነው፡፡ መንግስት ደግሞ የህግ የበላይነትን የማስከበር ብሎም የዜጎቹን ሰላማዊ ህይወት የመጠበቅ ኃላፊነትና መብት እንዲሁም ግዴታ ያለበት በመሆኑ ግለሰቡን በህግ ፊት ተጠያቂ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

እናም አቶ እስክንድር ህግና ስርዓትን በመጣስና ከጀርባቸው ልዮ የፖለቲካ አጀንዳን በማንገብ እንዲህ ዓይነቱን ግላዊ የመፃረር ተግባራትን ዳግመኛ በመፈፀማቸው እንዲሁም በምርጫ 97 ወቅትም ራሳቸው ህገ-መንግስቱንና ህገ-መንግስታዊ ስርዓቱን በኃይል ለመናድ መንቀሳቀሳቸውን አምነው በይቅርታ የተለቀቁበትን ጉዳይ ሆን ብለው ቸል በማለት በተመሳሳይ ፀረ-ህዝብ ድርጊት ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው ሊታሰሩ ችለዋል። ጉዳያቸውም በከፍተኛው ፍርድ ቤት ሲታይ ቆይቶ ጥፋተኛ ሆነው በመገኘታቸው ሳቢያም የ18 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸዋል። ተከሳሹም ጉዳዩን ወደ ፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቢወስዱም የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ አፅንቶታል።…ውድ አንባቢዎቼ እንግዲህ በጥቂት ትውስታዎቼ አቶ እስክንድር ማለት ምን ዓይነት ሰው እንደሆኑና የፍርዱንም ትክክለኛነት ሳትገነዘቡ የምትቀሩ አይመስለኝም።…አዎ! ግለሰቡ ሁከትና ብጥብጥን በማቀንቀን ግብረ-ሽበራን ለማከናወን ሲውተረተሩ እንደነበርና በዚህም ምክንያት ሀገራችን የዜጎቿን ሰላምና ደህንነት ለመጠበቅ ባወጣችው የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ተጠያቂ መሆናቸውን ብሎም ስራቸውን ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት በነፃነት የሚከውኑት የሀገራችን ፍርድ ቤቶች በወንጀለኛው ላይ በህጉ መሰረት ተገቢውን የቅጣት ውሳኔ መስጠታቸውን ቀደም ሲል ከጠቀስኩላችሁ ሁለት ማሳያዎች ብቻ እንደተረዳችሁ እርግጠኛ ነኝ።

እርግጥም መሬት ላይ ያለው ሃቅ ይህና ይህ ብቻ ነው። ግና ዕውነታው ይህ መሆኑ እየታወቀ፤ ‘ሲፒጄ የሀገራችንን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ለምን ለማጣጣል ከጀለ?፣ ለምን የኢትዮጵያን ፍርድ ቤቶች አሰራርን ነፃነት የሌላቸው አስመስሎ ለማቅረብ ሞከረ? ከጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ወደ ሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ ምደባ አፅዳቂነት ተሸጋግሮና ለይስሙላም ቢሆን የሚያራግበውን የስራ ገደቡን አልፎ አንድን ሉዓላዊት ሀገር በመዳፈር ማስጠንቀቂያ ቢጤ በመስጠት ወንጀለኛውን ግለሰብ በአስቸኳይ እንዲፈታ ለማዘዝ እንደምን ደፈረ?’ የሚሉትንና ቀደም ሲል የአቶ እስክንድርን የሁከት ፈጠራ አብነታዊ ትውስታዎቼን ለማየት ስንል በይደር ያቆየናቸውን ጉዳዩች እንድናነሳ ያደርገናል።

ምንም እንኳን የሲፒጄው የአፍሪካ ዳይሬክተር ሞሐመድ ኬይታ የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የወከሏቸው አባላት የሚገኙበት ፓርላማ መርምሮ ያፀደቀውን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግን ከድርጅታቸውም ይሁን ከራሳቸው ተግባርና ኃላፊነት ውጪ በሆነ መንገድ ለማጣጣል ቢሞክሩም፤ ሃቁ ግን እርሳቸው እንዳሉት አይደለም። በመጀመሪያ ደረጃ ሚስተር ኬይታ በአንድ ሀገር የውስጥ ጉዳይ /ለዚያውም የፍትሕ ጉዳይ/ ውስጥ ጣልቃ መግባት የሚችሉበት ህጋዊ መብት የላቸውም። ይህ ከፍተኛ ንቀት ነው። እርሳቸው ማውራት ያለባቸው የውሸት መጠሪያቸው ስለሆነው የጋዜጠኝነት መብት ተከላካይነት እንጂ ከልዩ የርዕዮተ-ዓለም ተልዕኳቸው

በመነሳት ስለ አንድ  ሀገር ህግ አይደለም። ግና ይህ የእርሳቸውም ይሁን የድርጅታቸው ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖም ቢሆን ፤የሀገራችን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ከዓለም አቀፉ ተመሳሳይ ህጎች ጋር ልዩነት ያለው አይደለም። አብዛኛው ክፍሉም ከምዕራቡ ሀገራት እንዳለ የተገለበጠ ነው ማለት ይቻላል። እናም ህጉም ይሁን የፍርድ ቤቶቹ ውሳኔ የሽብርተኝነትን ከባድ ወንጀል ያሳነሰም ሆነ ያገዘፈ አለመሆኑን በቅን ልቦና መገንዘብ ያስፈልጋል– የትም ሀገር ውስጥ ቢሆን ሽብርተኝነት ያው ሽብርተኝነት ነውና። የአፍሪካ፣ የአሜሪካ አሊያም የአውሮፓ ሽብርተኝነት የሚባል ነገር የለምና። መቼም በእነዚህ ሀገራት ውስጥ የሚገኙት ሽብርተኞች ቢሳካላቸው የሚያፈሱት የንፁሃን ሰዎችን ደም እንደመሆኑ መጠን፤ የተግባሩ አደገኛነት መለካት ያለበት ከዚህ ሃቅ አኳያ መሆኑን ሀገራችን ውስጥ የተፈፀመ አንድን ነገር ሲሰማ በውሃ ቀጠነ ማላዘን የሚወደው አክራሪ ተቋም ይስተዋል ብዬ አልገምትም።

ለነገሩ አንድ ሀገር ህግ ሲያወጣ በውስጡ ያሉትን መሰረታዊ ሃቆችን ተመርኩዞ የህዝቡን ሰላማዊ የህይወት መስተጋብር ለማረጋገጥ መሆኑን በጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ሽፋን የኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ተላላኪ ሆነውና እነርሱን ወክለው በሀገራችን ላይ የውሸት ክምር የሚደረድሩት ግለሰብና ድርጅታቸው መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል። ከዚህ አኳያ ሀገራችን ከድህነት አረንቋ ለመውጣት በከፍተኛ ትግል ላይ የምትገኝ መሆኗን ማጤን ያስፈልጋል። እናም ኢትዮጵያ የጀመረችው የዕድገትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ስኬታማ ሆኖ እንዲቀጥል፤ አስተማማኝ ሠላም የሰፈነበት ምህዳርን መፍጠር "ለነገ" የምትተወው ተግባር አይደለም፡፡ ለምን ቢባል፤ ለኢትዮጵያ ፈጣን ልማትን ማምጣትና ከተመጽዋችነት መላቀቅ "የሞት - ሽረት" ያህል የህልውና ጉዳይ በመሆኑ ነው፡፡ ታዲያ ሰላምን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ፤ ለብሔራዊ ደህንነቷ ስጋት የሆኑ እንቅስቃሴዎችን መከላከልና መቆጣጠር የግድ ይላታል፡፡

የሀገራችን የብሔራዊ ደህንነት ስጋቶች ናቸው ተብለው ከሚጠቀሱት ተግባሮች ውስጥ ደግሞ አንዱና ግንባር ቀደም ተጠቃሹ የሽብርተኝነት እንቅስቃሴ ነው፡፡ ሽብርተኝነት የራሱ መንስዔዎችና ዓላማዎች ቢኖሩትም፤ በውጤነት የሚያስከትለው አደጋ ግን አንድ ዓይነት መሆኑ ከማንም የተሰወረ ጉዳይ አይደለም፡፡ ምንም እንኳን እነ ሲፒጄ ተግባሩ የከፋ የሆነውን ይህን አደጋ እያወቁ ስውር የፖለቲካ አጀንዳቸውን ለማራመድ አሊያም ራሳቸውን ለመከላከልና ከተጠያቂነት ለመዳን ሲሉ ለህጉ የተጣመመ ትርጓሜ ቢሰጡትም፤ እውነታው ግን ሽብርተኝነት በየትኛውም የዓለም ክፍል ተቀባይነት የሌለው ህዝብ ጨራሽ ዘግናኝ የጭካኔ ተግባር መሆኑ ነው፡፡

ከሀገራችን አኳያም፤ ሽብርተኝነት የዜጎችን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚገታ፣ የመንግስትን የማስፈጸም አቅም የሚያዳክም ብሎም በሀገር ደረጃ የተጀመረውን የሠላም፣ የልማትና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታን የሚያደናቅፍ አሊያም የሚያጓትት አሉታዊ ውጤት ያለው አፍራሽ ተግባር

መሆኑ ይታመንበታል፡፡ ይህም በየጊዜው በሀገራችን ብሔራዊ ደህንነት ላይ የተቃጡ የሽብር ጉዳዮችንና ወደፊት ሊኖሩ በሚችሉ ስጋቶች ላይ ተንተርሶ የተያዘ ትክክለኛ አቋም መሆኑን መረዳት በጄ ነው፡፡ ከዚህ ዕውነታ በመነሳትም መንግስት የሀገሪቱንና የህዝቡን ሁለንተናዊ ደህንነት የመጠበቅ እንዲሁም በዓለምና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ከሽብርተኝነት አኳያ ያለበትን ኃላፊነትና ግዴታ ለመወጣት የፀረ - ሽብርተኝነት አዋጅን በቁጥር 652/2001 ማውጣቱን እውነትን ሰንቀው ሳይሆን በሀገራችን የዕለት እንጀራቸውን ለመጋገር የሚለፍፉት ሚስተር ኬይታ የገባቸው ሃቁ እንዲገባቸው የሚፈልጉ አይደሉም፡፡ ይሁንና ድርጅታቸው ሲፒጄ አዋጁን "በልጅ አመካኝቶ" እንዲሉ በአቶ እስክንድር ሰበብ በማጥላላት የተዳከመች ኢትዮጵያን ለማየት ካለው ድብቅ ፍላጎቱ በመነሳት፤ ለምን ሀገራዊ ደህንነታችሁን ትጠብቃላችሁ?፣ ለምንስ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ሃላፊነትና ግዴታችሁን ትወጣላችሁ? የሚል ከሆነ፤ ጉዳዮ ጭልጥ ያለ ፖለቲካዊ ይዘት ያለው ስለሆነ ሀገራችን የቅጥፈት ድርጊቱን ከመጋፈጥ ውጪ ሌላ አማራጭ ያላት አይመስለኝም። ምክንያቱም እንኳንስ መብትን አስከብራለሁ ባይ ተቋም ቀርቶ አሸባሪም ቢሆን የአንድን ሀገር ህዝብ በሽብርተኞች ለማስጠፋት እንዲህ አያስብምና። ያም ሆነ ይህ ግን አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም የኢፌዴሪ የህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ያወጣውን አዋጅ ለማጣጣል መከጀሉ፤ በህዝቡ ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነት ውስጥ ጣልቃ ገብቶ እኛ የሚያስፈልገንን አዋጅ እየመረጠልን ስለሆነ በፍፁም ተቀባይነት የለውም።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት የሚገባው ሌላው ጉዳይ ምንም እንኳን ስለ ሀገራችን ፍርድ ቤቶች አሰራር ሲፒጄ ባያገባውም፤ የሀገራችንን ስም ሆን ብሎ ለማጉደፍ ያነሳውና የኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች ነፃነት እንደሌላቸው ያሰፈረው አስገራሚ ልቦለዱ ነው። ግና ማንመ እንደሚያውቀው የሀገራችን ፍርድ ቤቶች ከየትኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት የራቁ፣ ስራቸውን በገለልተኝነት የሚከውኑና ከጊዜ ወደ ጊዜ አሰራራቸውን እያዘመኑ የመጡ ናቸው። ይህን ደግሞ ባህር ማዶ ቁጭ ብሎ ከመደስኮር ይልቅ በአካል ሀገር ቤት መጥቶ ማየት ይቻላል።...እናንተዬ እኔ የምለው በሲፒጄ እሳቤ "ጉዳይ አስፈፃሚው" አቶ እስክንድር ነፃ ካልተባሉ የፍርድ ቤቶች አሰራር "ነፃ አይደለም" ሊባል፣ በነፃ ከተለቀቁ ደግሞ "ነፃ ነው" ሊባል ነው ማለት ነውን?...እንዴት ነው ነገሩ?!...ምናልባት ሲፒጄ በትውልድ ሀገሩ አሊያም በሌላ ሀገር ውስጥ የሚያውቀው እንዲህ ዓይነቱን ፍርደ ገምድልነት ከሆነ ልምዱን እዚያው በፀበሉ ሊጠቀምበት ይችላል–እኛ ሀገር ውስጥ ከህግ የበላይነት ጋር የሚላተም የፍትህ ስርዓት የለምና።

የዚህን ፅሑፍ አቅራቢ እጅግ ያስገረመኝ ጉዳይ ሲፒጄ ራሱን ከጋዜጠኞች መብት ጠባቂነት ወደ የሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ መዳቢ አፅዳቂነት ከፍ ከማድረግ በዘለለ፣ "አቶ እስክንድርን ያለ አንዳች ቅድመ ሁኔታ ባስቸኳይ ልቀቁት" ያለው ቀልዱ ነው። እናም እኔም በበኩሌ ተቋሙን የጋዜጠኞች መብት ጠባቂ ወይስ የሀገራት የሰብዓዊ መብት ደረጃ አፅዳቂ? ስል

እጠይቃለሁ– ሁለቱንም እንዳልሆነ ባውቅም።…ግና እንዴት ነው ነገሩ እናንተዬ?...እነዚህ አክራሪ ኒዩ-ለበራል ኃይሎች ሳያውቁት ራሳቸውን ከመንግስታቱ ድርጅት ጋር አቻ አድርገው ይቆጥራሉ እንዴ?...እርግጥ አክራሪዎች ይህን ካላሉና እንደ ኢትዮጵያ ዓይነት በራሳቸው የልማት አቅጣጫ ተጉዘው ውጤታማ በመሆን ላይ የሚገኙ ሀገራትን በውሸት ካላብጠለጠሉ እንጀራ ገመዳቸው ስለሚበጠስ ከዚህ በላይም ቢሉ የሚገርም አይደለም።

የአንድ ሀገር የፍርድ ሂደት ወንጀለኛ ነው ብሎ የወሰነበትን ግለሰብ በአስገራሚ አጉራ ዘለልነት ምግባር “ነፃ ነው” ብሎ በመፈረጅ ለመቀልበስ የሚደነፋትም ከዚሁ የዳቦ ጉዳይ በመነሳት እንደሆነ ማንም ይገነዘበዋል። እናም የጥርስ አልባው ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ጣልቃ ገብነትና አላስፈላጊ መንጣጣት ከዚህ ሃቅ አኳያ የሚታይ ከመሆን በዘለለ፤ ጋዜጠኛም፣ ተንታኝም ሆነ ጦማሪ ላልሆኑት አቶ እስክንድር ያደረገው አሳፋሪ ሙግት ተሰማርቼበታለሁ ከሚለው ስራው ውጭ መሆኑን ያመለክታል–ዓላማው የርዕዩተ-ዓለም ትግል መሆኑን። ያም ሆነ ይህ ግን አክራሪው ቡድን አክራሪው ቡድን ማወቅ ያለበት አንድ ትልቅ ቁም ነገር አለ። እርሱም የሀገራችን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በታሪካቸው በፈለጉት የፖለቲ ህልዮት የመመራት ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤትነታቸውን እንኳንስ በአሉባልታ ቀርቶ በሌላም መንገድ ቢሆን ለማንም አሳልፈው ሰጥተው የማያውቁ መሆናቸውን ነው። ይህን ለማወቅ ደግሞ ድርሳናችንን በመጠኑ ገልበጥ፣ ገልበጥ ማድረግ ብቻ በቂው ይመስለኛል። እናም ቡድኑ እያንኳኳ ያለው የተሳሳተ በር መሆኑን አውቆ ምናልባትም የሚሰማው ካገኘ የቂራ ጩኸቱን ይዞ ሌላ አካባቢ ማንኳበብ እንዳለበት ሳልመክረው ማለፍ አልሻም። ቸር እንሰንብት።